# የጸጋው ቃል አማኞች

# ቤተ ክርስቲያን

## ድነት፡ አጭር የማስገንዘቢያ ጽሑፍ

አፕሪል 2017

<u>ኑረንበርግ</u>

# ኢየሱስ፡ የዘላለም ድነት ብቸኛው መንገድ

እግዚአብሔር ........ 1
ኢየሱስ ክርስቶስ ........ 2
መንፈስ ቅዱስ ........ 2
ቅዱስ መጽሐፍ ........ 3
የሰው ልጅና እና ኃጢአት ........ 3
ድነት (እምነት፣ ንስሐ እና ጸሎት) ........ 3
የሙታን ትንሣኤ ........ 5
ቤተ ክርስቲያንና ጥሪዋ/ ተልዕኮዋ ........ 5

የጸጋው ቃል አማኞች ቤተ ክርስቲያን

## እግዚአብሔር

አንድ ብቸኛና ሕያው የሆነ አምላክ አለ፡፡ እርሱም ሁሉን አዋቂ፣ ኀልው ስብዕና ያለው መንፈስ (Spiritual and personal being)፣ የሁሉ ፈጣሪ፣ ጠባቂ፣ አዳኝ እና የሰማይና ምድር ገዥ ነው፡፡ እግዚአብሔር በቅድስናው እና በችሎታው ፍጹምና ኃያል ነው፡፡ እግዚአብሔር ለእኛ በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ኀልው ሦስት አካላት (ሥላሴ) የተገለጠ ሲሆን በአገዛዝና በመለኮት ፍጹም አንድ አምላክ ነው፡፡ (ዘዳ 6፡4፤ መዝ 90፡2፤ መዝ 147፡5)

## ኢየሱስ ክርስቶስ

ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ የተፀነሰ፣ ከድንግል ማሪያም የተወለደ ፍጹም አምላክ እና ፍጹም የሆነ ሰው ነው፡፡ እርሱ ለኃጢአታችን ሥርየት በመስቀል ላይ ሞቷል፤ ከሙታንም መካከል በሦስተኛው ቀን በኃይልና በክብር ተነስቶ ወደ ሰማይ አርጓል፡፡ ኢየሱስ በሰው እና በእግዚአብሔር መካከል የሚገኝ ብቸኛው አስታራቂ ነው፡፡ የፈሰሰው የኢየሱስ ክርስቶስ ደም እና በክብር የተነሳበት የትንሣኤ ኃይል ለሚያምን ሁሉ ጽድቅ እና ድነት ለማግኘት ብቸኛ መሠረት ናቸው፡፡ እርሱ በሰው ልጆች ሁሉ ላይ ሊፈርድ እና መንግሥቱን ሊመሠርት እንደገና ይመጣል፡፡ (ሉቃ 1፣35፤ ሥራ 17፣31፤ ሮሜ 1፣3-4፤ ሮሜ 4፣24-25፤ ቆላ 1፣3-4)

## መንፈስ ቅዱስ

የእግዚአብሔር ቅዱሱ መንፈስ ዋነኛ አገልግሎት ኢየሱስ ክርስቶስን ማክበር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን በማጽናት ለመንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት ኃጢአተኞችን ዳግም ይወልዳል፣ ባመኑት ላይ ያድራል፣ ይመራል፣ ያሰለጥናል፣ በኃይል ይሞላል፡፡ ቅዱሱ መንፈስ በአማኞች ሕይወት በጸጋው ሙላት ይሠራል፡፡ እንዲሁም ሙሽራዪቱ ቤተ ክርስቲያንን እርግጥ ለሆነው የክርስቶስ ዳግም ምጽዐት ያዘጋጃታል፡፡ (ዮሐ 3፣5፤ ዮሐ 16፣5-14፣ ኤፌ 5፣18፤ ቲቶ 3፣4-5)

የጸጋው ቃል አማኞች ቤተ ክርስቲያን

## መጽሐፍ ቅዱስ

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በመረጣቸው ቅዱሳን፣ በመለኮታዊ ኃይል (በመንፈስ ቅዱስ/ በእስትንፋሰ መለኮት) እርዳታ የተጻፈ መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፉ እግዚአብሔር ራሱን ለሰዎች በትክክል የገለጠበት ነው፡፡ የመጽሐፉ ደራሲ እግዚአብሔር ሲሆን ቅዱሳኑ በመንፈስ በመመራት (በመነዳት)፣ ያለምንም ስህተት የፃፉትም ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ ሰዎች እምነታቸውን፣ ግብረ ገብን (መልካም ምግባርን) እና ሃይማኖታዊ አመለካከቶቻቸውን የሚያስተካክሉበት መለኪያ ነው፡፡ መጽሐፉን በአግባቡ የመተረጎሚያው መስፈርት ሥጋ ሆኖ የተገለጠው መለኮት - ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፡፡ (2ኛ ጴጥ 1፥20-21፤ ዮሐ 5፥39-40)

## የሰው ልጅና እና ኃጢአት

ሰው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ (image and likeness) የተፈጠረ የእርሱም የእጅ ሥራ ውጤት ነው፡፡ በመጀመሪያ ሰው ከኃጢአት የነጻ ነበር፡፡ ነገር ግን ሰው በነጻ ፈቃዱ በእግዚአብሔር ላይ በማመጹ ኃጢአትን አደረገ፡፡ ሰው በኃጢአቱ ምክንያት መንፈሳዊ እና አካላዊ ሞትን ወደ ራሱ አመጣ፡፡ (ዘፍ 1፥26-28፤ ዘፍ 2፥7/ 16-17)

## ድነት (እምነት፣ ንስሐ እና ጸሎት)

ድነት በእግዚአብሔር ጸጋ በእምነት፣ ክርስቶስን በመቀበል፣ ንስሐ በመግባት (ለኃጢአት ይቅርታ በመጠየቅ) የሚገኝ የዘላለም

ሕይወት ነው፡፡ ጸሎት ደግሞ ለአምላክ ምስጋና፣ ልመና እና ምልጃ የሚቀርብበት ግንኙነት ነው፡፡ (ሮሜ 6፣22-23፤ ምሳ 28፣ 13፤ ማቴ 3፣8)

ሰፋ ባለ መልኩ ሲዳሰስ ድነት የአማኝን ዳግም ውልደት፣ መጽደቅ እና መክበር በሚከተለው መልክ የሚገልጽ ነው፡፡ ይኸውም፡

- <u>ዳግም ውልደት</u>/ <u>ዳግም ልደት</u> ወይም <u>ጽድቅ</u>፡- በእምነት አማካይነት የሚገኝ በእግዚአብሔር ጸጋ ለአማኝ የሚሰጥ ነው፡፡ ዳግም ልደት በመንፈስ ቅዱስ የሚቸር የልብ መለወጥም ሲሆን ዐዲስ አማኝ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን በንስሐ ወደ እግዚአብሔር መመለስ ማለት ነው፡፡ ዳግም ውልደት በክርስቶስ ኢየሱስ ያመነ አማኝ የውኃ ጥምቀት በማድረግ በክርስቶስ ማመኑን የሚያሳይበትና ከኢየሱስ ትንሣኤ ጋር መተባበሩን የሚያስመሰክርበትም መነሻ ነው (ሮሜ 6፣3፤ ማቴ 28፣19)፡፡

- <u>መቀደስ</u>፣ መቀደስ በዐዲስ ልደት (በጽድቅ) የሚጀምር ሂደት ሲሆን አማኙ በእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ መገኘትና ኃይል ለእግዚአብሔር የዘላለም ማዳን ዓላማ መለየትን እና በመንፈሳዊ ሕይወት ወደ ፍጽምና መድረስ ነው፡፡ ቅድስና በእግዚአብሔር ጸጋ ዐዲስ በተወለደው ግለሰብ ውስጥ ያለማቋረጥ ያድጋል/ ይጨምራል፡፡ (1ኛ ቆሮ 6፣11፤ 2ኛ ቆሮ 7፣1፤ 1ኛ ተሰ 5፣23-24)

- <u>መክበር</u>፣ መክበር የመዳን ፍጻሜ/ መደምደሚያ እና የአማኝ የመጨረሻ የበረከት እና የተስፋ ቃል ፍጻሜ ነው፡፡ (ሮሜ 8፣30)

## የሙታን ትንሣኤ

በቅዱሳን መጽሐፍት እንደተጻፈው ሙታን እንደሚነሱ እናምናለን፡ ይኸውም አማኞች ለዘላለም ከጌታቸው ጋር በረከትና ተድላ ይቀዳጃሉ፣ የማያምኑ ግን የዘላለም ፍርድ ቅጣት ይቀበላሉ፡፡ (ዮሐ 11፣24-27፤ 1ኛ ቆሮ 15፣51-52)

## ቤተ ክርስቲያንና ጥሪዋ/ ተልዕኮዋ

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እግዚአብሔርን የሚያመልኩ፣ ኅብረት የሚያደርጉ፣ የሚጸልዩ እና በኅብረት የሚገለገሉ አማኞች ቤተሰብ (ስብስብ) ናት፡፡ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ጌትነት እና በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የምትንቀሳቀስ ናት፡፡ ቤተ ክርስቲያን የምትኖረው አዳኟን በግል እና በኅብረት አምልኮ ለማግነን/ ለማላቅ እና ለማክበር ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ሁላችን በእምነት አንድነት እና በእግዚአብሔር ልጅ በክርስቶስ ኢየሱስ እውቀት ማደግ፣ ፍጹም ክርስቶስንም መምሰል እንዲችሉ በቅዱሳን ድርሳናት (scriptures) እውቀት የማሰልጠን/ የማስታጠቅ እና በክርስቲያናዊ ኅብረት የማጎልመስ ኃላፊነት አለባት፡፡ (1ኛ ቆሮ 1፣2/9፤ ማቴ 28፣19-20)

የጸጋው ቃል አማኞች ቤተ ክርስቲያን